የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵፫
አዲስ አበባ ሰኔ ፲ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 43
ADDIS ABABA 17th June, 2013


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፫/፪ሺ፭ ዓ.ም

ከኳታር መንግስት ጋር የተደረገው የሥራ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ........................ገጽ ፮ሺ፰፻፹፬


CONTENTS


Proclamation No. 793/2013

Labour Agreement with the Government of the State of Qatar Ratification Proclamation ..... ........................................................ Page 6884


## አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፫/፪ሺ፭

## ከኳታር መንግስት ጋር የተፈረመውን የስራ ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኳታር መንግስት መካከል ለኢትዮጵያ ዜጐች በኳታር የሥራ እድል የሚያስገኘው ስምምነት ህዳር ፳፭ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም በዶሃ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፱ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ከኳታር መንግስት ጋር የተደረገው የሥራ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፫/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION No. 793/2013

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LABOUR AGREEMENT WITH THE GOVERNMENT OF THE STATE OF QATAR

WHEREAS, the Agreement concerning the Employment of Ethiopian Manpower in the State of Qatar between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the State of Qatar was signed in Doha on the 4th day of December, 2012;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 6th day of June, 2013;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Labour Agreement with the Government of the State of Qatar Ratification Proclamation No. 793/2013".


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazette P.O.box 80,001

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኳታር መንግስት መካከል ህዳር ፳፭ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም. በዶሃ የተፈረመው ለኢትዮጵያ ዜጎች በኳታር የሥራ እድል የሚያስገኘው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሥልጣን

ይህ ስምምነት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፲ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Agreement

The Agreement concerning the Employment of Ethiopian Manpower in the State of Qatar signed in Doha on the 4th day of December, 2012 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the State of Qatar is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Labour and Social Affairs

The Ministry of Labour and Social Affairs is hereby empowered to implement the Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of June, 2013.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት